በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መጽሐፈ ነህምያ - ክፍል ፫


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጥቅምት ፲፯ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፩

- ዛሬ መጽሐፈ ነህምያን ከመሪነት አንጻር ማጥናት የጀመርንበትን ትምህርት አምስተኛ ክፍል እንመለከታለን። ይልቁኑ በዓለም፣ በቤተ ክርስቲያንም ሳይቀር ከፍተኛ የመሪዎች እጥረት ባለበት በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ሁሉ ለመሪነት እንዲበቁ የመሪነት ችሎታ እንዲያዳብሩ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚመሩ እንዲሆኑ ይሻል። እግዚአብሔር ሁላችንም የመሪነትን ስጦታና ብቃት እንዲሰጠን ፈቃዱ ይሁንልን።
- ነህምያ የንጉሡ ጠጅ አሳላፊ ሆኖ በፋርስ ይኖር ነበር። የእስራኤል ልጆች ይልቁንም ብርቱዎቹ በናቡከደነፆር ተማርከው ተወስደው ነበር፤ በቤተ መንግሥቱም ያገለግሉ ነበር።
- ነህምያ በንጉሡ ቤተ መንግሥት የሚሠራ ቢሆንም ልቡ ግን በኢየሩሳሌም ነበር፤ ቅጥሮችዋም መፍረሱን ሲያውቅ ለመገንባት የንጉሡን ፈቃድ ጠይቆ ቁሳቁስና ጠባቂዎችን አስከትሎ በኢየሩሳሌም ያለውን ሁኔታ ለመመርመርና ቅጥሮችዋንም ለመሥራት ተጓዘ፤ ታላቅ ዝግጅትም አድሮጎ ቅጥሩን መሥራት ጀመረ።
- ሥራውን የጀመረው ተሰናድቶ፣ አደራጅቶ፣ ከንጉሡም ወታደሮችን አስከትሎ፣ በመጾም፣ በመጸለይ… ነበር። ነገር ግን የእነዚህ መሟላት ሥራውን ያቀለዋል ማለት አይደለም። በመጽሐፈ ሲራክ ‹‹ልጄ ሆይ እግዚአብሔርን ታገለግለው ዘንድ ብትወድ ሰውነትህን ለመከራ አዘጋጅ።›› እንዳለ መከራና ፈተና አለና።
- እግዚአብሔርን ለማገልገል በጎ ሥራንም ለመሥራት ስንነሳ ችግር፣ ነቀፋ፣ ወደ ኋላ ማለት (መመለስ)፣ ስለሚያጋጥመን በሩ ሁሉ ክፍት ሆኖ ሰዎች ሁሉ በቅንነት እንደሚደግፉንና እንደሚቀበሉን አድርገን አንጠብቅ።
- ምክንያቱም እግዚአብሔርን ለማገልገል ለመንግሥቱም ለመሥራት ስንነሳ እንቅስቃሴያችን ሁሉ በቀጥታ ዲያቢሎስን መቃወም፣ ከሁሉ የተለየ ጠላቶቹ ሆነን ወደ ውጊያው ቀይ ቀጣና መግባት ነውና።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

- በዚህም ምክንያት ነህምያ ሥራውን ሲጀምር በርካታ ተቃውሞና ነቀፋ እንዲሁም ወደ ኋላ የሚመልስ እንቅፋት ጠበቀው። ነገሮቹ እንደታቀዱት አልቀጠሉም፣ ቀላልም አልሆኑም፣ ሕዝቡም በኢየሩሳሌም ዙሪያ የቅጥሩ ግንባታ ከፍ ብሎ ሲያዩ እንደተጠበቀው ደስተኛ ሆነው አልተገኙም።
- ሕዝብ ይህን ሁሉ በቀላሉ አይረዳም፤ ቀድሞ የሚታየው እንቅፋቱ ተቃራኒ ነገሩ ነው። ባለፈው ሳምንት መሪ ነቀፋ እንደሚጠብቀውና ለነቀፋ እንዴት መዘጋጀት እንዳለበት ተምረናል። ዛሬ ደግሞ ወደ ኋላ ስለ ማለት እንማራለን። በሕይወታችን አንድን መልካም ሥራ ችግሮችን ሳንጋፈጥ ወይም ወደ ኋላ የሚያሰኝ ነገር ሳይገጥመን እንደማንሠራ ፈጽመን አንዘንጋ። ዛሬ የምንማረው ይህንን ነው።
- ቶማስ ኤዲሰን በርካታ የፈጠራ ሥራዎችን ያከናወነ (አምፑል፣ ስልክ፣ ፊልም፣...ኤሌክትሪክሲቲ) አሜሪካ ከምትኮራባቸው ሰዎች አንዱ ነው። በ1914 በ67 ዓመቱ ሥራዎቹን በሚሠራበት ቤተ ሙከራ ውስጥ ባትሪዎችን የመሞከር (የመፈተሽ) ሥራ ይሠራ ነበር። የአጼ ምኒሊክ መኪና እንዴት እንደምትሠራ አይተናታል? ታዲያ ለታላቅ መኪኖች የሚሆን ባትሪ ሲሞክር ባትሪው ፈንድቶ ታላቅ እሳት ተነስቶ ቤተ ሙከራውን፣ መፈተሻውን፣ ዕድሜውን ሙሉ የደከመበትን ሥራና የሥራ ውጤት ሁሉ አወደመው። ልጁንም ሲሮጥ አይቶት እናትህ ወዴት ናት? ብሎ ሲጠይቀው ልጁም በመኖሪያ ቤታችን ውስጥ ናት አለው። ቶማስም ልጁን እናትህ በዕድሜዋ (በዘመንዋ) ሁሉ ፈጽማ ልታየው የማትችለውን የእሳት ነበልባል ታይ ዘንድ ፈጥነህ ጥራት አለው። ቶስ እጅግ ቀና ሰው ነበር። በ67 ዓመቱ፣ በጡረታ ጊዜው ራሱን ወደ ፍሎሪዳ ሂድ፣ የሕይወትን ጣዕም በዚያ አጣጥም አላለውም። በብዙ ድካም በሚቀጥለው ቀን እሳቱን አጠፋው። ሠራተኞቹንም ሰብስቦ፣ በርግጥ በእሳቱ የተነሳ መጥተው ነበር ‹‹አሁን የወደመብንን ሁሉ መልሰን እንገነባዋለንና ክሬይኑን፣ የግንባታ ሞያተኞቹን፣ የእቃ አከራዮችን ጥሩልኝ።›› አላቸው። ከዚህ በኋላ ነው በርካታ የፈጠራ ሥራዎቹን የሠራው፤ በዚህም የተነሳ እንዲህ ያሉ ከባድ አጋጣሚዎች ለአዲስ ለውጥ የሚያነሳሱ ናቸው በማለት እንደገና ከ67 ዓመቱ በኋላ በርካታ ሥራዎችን ሠራ። ተስፋ ቆርጦ ወደኋላ እንዲመለስ የተፈጠረው አጋጣሚ አላሸነፈውም ቀጥሎ ታላቅ ሥራን ሠራ እንጂ።

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፩</u>

- ነህምያ ምሳሌ የሆነውም በዚህ ሕይወቱ ነው፤ ተስፋ ሳይቆርጥ ወደ ኋላም ሳይል መልሶ ኢየሩሳሌምን በመገንባት ሥራው ቀጠለ፡፡
- ‹‹ ይሁዳም። የተሸካሚዎች ኃይል ደከመ፥ ፍርስራሹም ብዙ ነው ቅጥሩንም እንሠራ ዘንድ አንችልም አሉ። ጠላቶቻችንም። ወደ መካከላቸው እስክንመጣና እስክንገድላቸው ድረስ ሥራቸውንም እስክናስተጓጕል ድረስ አያውቁምና አያዩም አሉ። በአጠገባቸውም የተቀመጡት አይሁድ መጥተው። ከስፍራው ሁሉ ይመጡብናል ብለው አሥር ጊዜ ነገሩን።›› ***<u>ነህ 4፡10፡፡</u>*** ብለው
- ይሁዳ የእስራኤል መሪ የሆነ ነገድ ነው፤ ይሁን እንጂ ተስፋ የሚያስቆርጥ ወደ ኋላም የሚያሰኝ ነገር አመጡ፡፡ ፍርስራሹ ብዙ ነው፤ ሥራውም ብዙ ነው፤ ሥራውንም እንድንሠራ ጠላቶቻችን አይፈቅዱልንም መጥተው ይገድሉናል ያጠፉናልም ይህንንም በአጠጋባቸው ሆነው ያሉ ወገኖቻችን አይሁድ ነግረውናል አሉ፡፡ የይሁዳ ነገድ መሪ ነገድ ቢሆንም የቻልነውን ሞክረና፤ ማድረግ የምንችለው ይህንን ነው፤ የኛን ድርሻ ተወጥተናል ይበቃል አሉ፡፡ ተስፋ ያስቆረጧቸው ወደ ኋላ የመለሷቸው ምክንያቶች ምንድር ናቸው? አራት ምክንያቶች ወደ ኋላ መልሰዋቸዋል፡፡

## 1. <u>ጥንካሬ ማጣት</u>

- የመጀመሪያው ጥንካሬ ማጣት ነው ‹‹ ይሁዳም። የተሸካሚዎች ኃይል ደከመ፡፡›› ***<u>ነህ 4፡10፡፡</u>*** እንዳለ፡፡ አብቅቶለታል ምንም መሥራት አንችልም አሉ፡፡ የቅጥሩ ሥራ *<u>በነህ 4፡6</u>* እንደምናነበው በከተማዋ ዙሪያ እስከ እኩሌታ ደርሶ ነበር፡፡
- እኛም በምንሠራው ሥራ እኩሌታ ላይ ተስፋ መቁረጥ እንደሚያጋጥመን እናውቃለን? ግን ለምን? ምክንያቱም በቅድሚያ ለመጀመር በበርታት እንነሳሳለን፣ ሲጠናቀቅም እንዲሁ ነው፤ ዋናው ችግር መሐል ላይ ነው፡፡ በርካታ ሰዎች በትምህርት፣ በትዳር፣ በፕሮጀክቶቻቸው መሐል ደርሰው እጅ ይሰጣሉ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

## 1. ጥንካሬ ማጣት…

- በብድር የገዛናትን መኪናችንን ከሁሉም በላይ የምንጠላው መቼ እንደሆነ እናውቃለን? አዲስነትዋ ሲያልፍበት ጠረንዋ ሲለወጥ፣ ዕዳችንንም ለመክፈል መሐል ላይ ስንደርስ ነው። እስከግማሽ ከፍለና ከዚህም በኋላ ክፍያው ግማሽ መንገድ እንደቀረው ስናረጋግጥ እጅ እንሰጣለን፣ ያስጠላናል፤ መቼ ይሆን ይህ ክፍያ የሚያልቀው እንላለን።
- ሁላችንም መካከል ደርሰን እንፈተናለን፤ ዋነው ነገር ‹‹እንቀጥላለን ወይስ አንቀጥልም›› ነው። መካከል ደርሰን ጉልበት እናጣለን፣ ደክሞኛል፣ አልችልም፣ ከዚህ በኋላ አልቀጥልም… እንላለን።

## 2. ራእይ ማጣት

- ‹‹ ፍርስራሹም ብዙ ነው፡፡›› ***ነህ 4፡10፡፡*** እንዳለ ወደ ሚሠሩት ቅጥር ሳይሆን ወደ ፍርስራሹ ተመለከቱ። የቅጥሩ ሥራ ተጠናቆ እስራኤልም ብርቱ፣ ታላቅ አገር ኢየሩሳሌምም ውብ መሆንዋን፣ ንግዳቸው ተስፋፍቶ የምትደነቅ፣ የቤቶቻቸው ዋጋ ማደጉን፣ አገርዋ መለወጥዋን ሳይሆን ፍርስራሹን ተመለከቱ።
- በርካታ ሰዎች ተስፋ የሚቆርጡት እጅ የሚሰጡት በዚሁ የተነሳ ነው። ታላላቅ እድሎች ለሥራ ወይም ለአገልግሎት የሚገጥሙአቸው በርካታ ሰዎች የሚያስቆጡ ወይም የሚያበሳጩ (ፍርስራሽ) የሥራ ወይም የአገልግሎት አጋሮቻቸውን ድራማ ይመለከታሉ። ያለን አቅም፣ እድል ወዴት አለ? እግዚአብሔር ወደ ሚመራን፣ እንድንገኝ ወደ ሚፈልገው ቦታ ሳይሆን በርካታ ፍርስራሾች ወዳሉበት እንመለከታለን። ይህም ሰዎችን ተስፋ ወደ መቁረጥ እጅ ወደ መስጠት እንዲያመሩ ያደርጋቸዋል።

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫</u>

## 3. *<u>በራስ መተማመንን ማጣት</u>*

- ‹‹ቅጥሩንም እንሠራ ዘንድ አንችልም አሉ።›› ***<u>ነህ 4፡10፡፡</u>*** እንደተባለ፡፡ የተወደዳችሁ ምዕመናን የምንናገው ምን እንደሆነ በአግባብ እናስተውል!!!
- ብዙ ጊዜ የምንናገረው ነገር ለብርታታችን ወይም ለድክመታችን ትንቢት ነው፡፡ አደርገዋለሁ ካልን በፈቃዱ እናደርገዋለንና፡፡ አንዳንድ ጊዜ ዲያቢሎስ በአንደበታችን ያላስተዋልነውን ነገር ያናግረናል፡፡ ለምሳሌ አንድ ችግር ገጠማችሁ እንበል፤ ስለዚያ ችግር ላገኛችሁት ጓደኛችሁ አወራችሁለት፤ ንግግራችሁን እየቀጠላችሁ ስትሄዱ የበለጠ ንዴታችሁ እየጨመረ ሄዶ ራሳችሁን ወይም ያገኛችሁትን ነገር እስክትመቱ ድረስ ትደርሳላችሁ፡፡ ታዲያ ይህን ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ንግግራችንና ንዴታችን እየጨመረ ሲሄድ ከራሳችን አንደበት መውጣት የሌለበትን እስከመናገር እንደርሳለን፡፡ ስለዚህ ከእምነታችን የተገኘ መልካም ቃል ካልሆነ በቀር ሌላ ከአንደበታችን እንዲወጣ ፈጽመን አንፍቀድ፡፡
- ይህም ማለት መሥራት አልችልም፣ ሰይጣን አሳሳተኝ፣ ይበዛብኛል፣ አስተካክዬ ልሠራው አልችልም… የሚሉ ጎጂ ቃላቶች ከመጠቀም እንቆጠብ፤ በአእምሮአችን ቢመላለስም እንኳ በአንደበታችን ከመናገር እንቆጠብ፡፡
- ሠራተኞቹም ‹‹ቅጥሩንም እንሠራ ዘንድ አንችልም።›› ካሉ በኋላ በራስ መተማመናቸውን አጡ፡፡ ማታ ደክሞኝ አቅቶኛል ብንልም ጠዋት እሠራዋለሁን አንርሳ፡፡ እጅ መስጠት ጥልቅ ስሜት የሚያስከትለው ጉዳት ነው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፳

## 4. *የደህንነት ስጋት*

- ‹‹ጠላቶቻችንም። ወደ መካከላቸው እስክንመጣና እስክንገድላቸው ድረስ ሥራቸውንም እስክናስተጓጉል ድረስ አያውቁምና አያዩም አሉ።›› ***ነህ 4:11።***
- ደህንነታችን ከምን ውስጥ ነው? ከሥራችን? ከጓደኞቻችን መካከል ነው? በምቾት መንደራችን ነው? በከተማችን ውስጥ ነው? በነገሮቻችን መካከል ነው? በተለያዩ ልምምዶቻችን መካከል ነው? እነዚህስ ነገሮች ቢወሰዱብን ተስፋ የመቁረጥ እጅ የመስጠት ስሜት ይሰማናል?
- አንዳንድ ጊዜ በፊታችን የተዘረጋው ሥራ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ስኬትን ቢሰጠን፣ ቢረዳን፣ ከግማሽ መንገድ ቢያደርሰንም እንኳ እጅ የመስጠት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን።
- ይህም መንገዳችን ጥንካሬ፣ ራእያችንን፣ በራስ መተማመናችንን አሳጥቶ ፍርሐት ውስጥ ጥሎ እጅ ወደ መስጠት ያደርሰናል። ይህ የእያንዳንዳችን ችግር ሊሆን ይችላል፤ በቃኝ፣ ኧረ ምን አደከመኝ፣ ምን አጨቃጨቀኝ? ብለን የጀመርነውን የእግዚአብሔር ሥራ አልተውንምን?
- ነህምያ እናንተ ሕዝቦች ሁሉን አቀረብኩ፣ አደረግሁ፣ መሥራት አልወደዳችሁም፤ እንግዲያውስ መሥራትን ትታችሁ በዚሁ ሁኔታ መኖር ከፈለጋችሁ ቀጥሉበት እኔ ወደ ፋርስ ተመልሼ በምቾት ቤተ መንግሥትም እኖራለሁ አላለም፤ ሥራውን ቀጠለ እንጂ።
- ***ነህምያ እጅ መስጠትን እንዴት አሸነፈው? አምስት መንገዶችን (አቅጣጫዎችን) ተከትሎ ተስፋ መቁረጥን እጅ መስጠትን ወደ ኋላ ትቶ ሥራውን ወደ ፊት ቀጠለ።***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

## 1. ጥረቶቹን በሙሉ በአንድነት ወደ ግቡ ማድረግ

- ‹‹ ከቅጥሩም በስተ ኋላ በኩል ባለው በታችኛው ስፍራ ሰይፋቸውን ጦራቸውንም ቀስታቸውንም አስይዤ ሕዝቡን በየወገናቸው አቆምኋቸው።›› ***ነህ 4፡13፡፡***
- ብዙ ጊዜ እጅ የሚያሰጡ ፈተናዎችን በቸልታ አልፈን እስኪጥሉን ድረስ እድል እንሰጣለን፡፡ የመኪናችን ጎማ ሲተነፍስ ዝም ብለን ብንነዳው የሚፈጠረው ምንድን ነው? መኪናውን እስከመቃጠል በኛም አደጋ እስከማስከተል ያደርሰዋል፡፡ ስለዚህ ቶሎ ቀመን ጎማችንን መቀየር አለብን፡፡
- ነህምያም ሥራውን አቁሞ፣ ሰዎችን ከቤተሰቦቻቸው ጋር አደራጀ፣ የሚግባቡበትን መንገድ አመለከተ፣ መበርታት እንዳለባቸው ነገራቸው፣ እያንዳንዳቸው የሚሰሩበትን ቦታ አመለከታቸው፡፡
- ከዚህ የምንረዳውም እረፍት ወስደን፣ ራሳችንን ከጠላት የምንታደግበትን የግለኝነት መንገድ ትተን ሊያግዙን የሚችሉትን እንለይ፣ እንደሚገባቸው እንመድባቸው በየወገናቸው እናቁም፡፡

## 2. ትኩረታችንን ወደ እግዚአብሔር እናድርግ

- ‹‹ አይቼም ተነሣሁ፥ ታላላቆቹንና ሹማምቱንም የቀሩትንም ሕዝብ። አትፍሩአቸው ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ፥ ስለ ወንድሞቻችሁም ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች ልጆቻችሁም ስለ ሚስቶቻችሁም ስለ ቤቶቻችሁም ተዋጉ አልኋቸው።›› ***ነህ 4፡14፡፡***
- ብዙ ጊዜ እጅ የሚያሰጥ አጋጣሚ ቢፈጠርም ትኩረታችንን ከራሳችን ወደ እግዚአብሔር እናድርግ፡፡ ይህም ማለት ቃል ኪዳኑን አስቡ ማለት ነው፡፡
- ‹‹በአንተ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ። ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም አምባ ነውና ለዘላለም በእግዚአብሔር ታመኑ።››***ኢሳ 26፡3-4፡፡*** እንደተናገረው ዓይናችንን ከፍርስራሹ አንስተን ጌታን እናስብ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፰

## 2. *ትኩረታችንን ወደ እግዚአብሔር እናድርግ…*

- **ሌላው የሚያስተምረን ጥቅስ** ‹‹ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል። በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ፤›› ***ፊል 4፡6-8፡፡***
- **እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ያደረገላችሁን አስቡ፤ ጌታንም አስቡት፡፡ ‹‹ተስፋ ስትቆርጡ ጌታን አስቡ፡፡›› እነዚህን አራት ቃላት ዘወትር ልብ እንበል፤ ትኩረታችንን ወደርሱ ይመልሳልና፡፡**
- **ቀድመው ትኩረታቸው በድክመታቸው ላይ ነበር፤ ባልቻሉት አቅም ባጡበት ነገር ነበር፤ ጌታን ቢያስቡት በመካከል መጣላቸው፡፡**

## 3. *በምናስበውና በምንሠራው መካከል - ሚዛናችንን እንጠብቅ*

- **ተበረታቱ ተነሡ ጌታንም አስቡ አለና** ‹‹ጠላቶቻችንም ይህ ነገር እንደ ደረሰልን፥ እግዚአብሔርም ምክራቸውን ከንቱ እንዳደረገው ሰሙ እኛም ሁላችን ወደ ቅጥሩ እያንዳንዳችን ወደ ሥራችን ተመለስን። ከዚያም ቀን ጀምሮ እኩሌቶቹ ብላቴኖቼ ሥራ ይሠሩ ነበር፥ እኩሌቶቹም ጋሻና ጦር ቀስትና ጥሩርም ይዘው ነበር አለቆቹም ከይሁዳ ቤት ሁሉ በኋላ ይቆሙ ነበር። ቅጥሩንም የሚሠሩትና ተሸካሚዎቹ በአንድ እጃቸው ይሠሩ ነበር፥ በአንድ እጃቸውም የጦር መሣሪያቸውን ይይዙ ነበር። አናጢዎቹም ሁሉ እያንዳንዱ ሰይፉን በወገቡ ታጥቆ ይሠራ ነበር ቀንደ መለከትም የሚነፋ በአጠገቤ ነበረ።›› ***ነህ 4፡15-18፡***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

## 3. ***በምናስበውና በምንሠራው መካከል - ሚዛናችንን እንጠብቅ...***

- እግዚአብሔርን ማመን መልካም ቢሆንም የራሳችን ድርሻ የሆነውን ሥራ ግን መሥራት አለብን፡፡ መጸለይ፣ ዘወትር ተደጋግሞ የሚሠራውን አለማቋረጥ፣ መታገል፣ በተቻለን መጠን የሚሻለውን ማድረግ መልካም ነው፡፡ በራሳችን በኩል ድርሻችን የሆነውን ሥራ ሳናቋርጥ እግዚአብሔር እንዲያበረታን መጠበቅ አለብን፡፡
- ዘወትር በመጸለይ፣ በማለዳ ተነስተን ወደ ቤቱ በመገስገስ፣ ቃሉን በማንበብ፣ ከእንቅልፍ ዘግይተን በመሥራት የጦር እቃችንን ይዘን እግዚአብሔር እስኪያበረታን ስለምን አንጠብቀውም?
- ሕዝቡ ጸለዩ፣ መሣሪያዎቻቸውን ተሸከሙ ወዲያውም ሥራቸውን በአንድ ጊዜ አብረው ሠሩ፡፡ በዚህ መንገድ ሚዛናችንን ጠብቀን መራመድ ይኖርብናል፡፡ ከማመን ጋር ቀኖናችንንና ሥርዓታችንን መጠበቅ ፤ ከመማር ጋር ማስቀደስ ንስሐ መግባትና መቁረብ አለብን... ሚዛን መጠበቅ ይገባልና፡፡
- ሳንሠራ እግዚአብሔር እንዲጠብቀን የምንሻ፤ ወደ ፈተና እንዳንገባ በጸሎት፣ በጾም፣ በማስተዋል ራሳችንን ሳንጠብቅ እግዚአብሔርን ለማገልገል የምንሰለፍ ከሆንን እንደምንወድቅ እንወቅ፡፡
- በጸሎት በአገልግሎት ብርቱ ልንሆን እንችላለን ይህን ብቻ ይዘን የምናገለግል ከሆን መሣሪያውን ሁሉ በመሸከም ብርቱ አይደለንም፡፡ ‹‹ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ፡፡›› ***ኤፌ 6፡11፡፡*** እንደተባልን በክፉ ቀን በርትተን እንድንገኝ የእግዚአብሔርን የጦር እቃ ሁሉ እንልበስ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

## 3. ***በምናስበውና በምንሠራው መካከል - ሚዛንን መጠበቅ…***

- የእግዚአብሔርን የጦር እቃ በመልበስ በጸሎትና በጾም በርትተን በማገልገል እግዚአብሔር የሰጠንን ጸጋ እንዴት መጠበቅ እንዳለብን እናውቃለን?
- ስንሠራ መሣሪያውን እንሸከም፣ ስናገለግል በመንፈሳዊነት ነገሮችን እንመርምር እናስተውል! ይህ እጅግ አስፈላጊና እጅ መስጠትን የምንዋጋበት መንገድ ነው፡፡

## 4. ***የምናደርገውንና የሚደርግልንን አስተዋጽዖ ለይተን እንወቅ***

- ‹‹ታላላቆቹንና ሹማምቱን የቀሩትንም ሕዝብ። ሥራው ታላቅና ሰፊ ነው፥ እኛም በቅጥሩ ላይ ተበታትነናል፥ አንዱም ከሁለተኛው ርቆአል  የቀንደ መለከቱን ድምፅ ወደምትሰሙበት ስፍራ ወደዚያ ወደ እኛ ተሰብሰቡ አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል አልኋቸው።›› ***ነህ 4፡19-20፡፡***
- ከዚህ የምንወስደው መርህ በራሳችን ለመሥራት እንዳንሞክር ነው፡፡ በተለይ ለምን ይቅርብን ብላችሁ በክህነት (መቅደሱ) አገልግሎት ጉዳይ እጃችሁን አታስገቡ፤ አትድፈሩ፤ ትወድቃላችሁና፡፡
- ያለ እግዚአብሔር በራሳችን ማድረግ እንደማንችል እስክንማር ድረስ እንወድቃለን፡፡
- ታዲያ ቤተ ክርስቲያን ንስሐን፣ ምስጢራትን፣ የቅዳሴ አገልግሎቱን ቅዳሴውን ስለምን አዘጋጀችልን? አብረን እንድናመልክ፣ እንድናገለግል አይደለምን! በርግጥ ሁላችንም አንዳችን ላንዳችን እናስፈልጋለን፤ እንፈላለጋለንም፡፡
- ነህምያ የቀንደ መለከቱን ድምፅ ስትሰሙ በዚያ ተሰብሰቡ አላቸው፤ በራሳችን ስለማናደርገው እርዳታ ስለሚያስፈልገን!!! እግዚአብሔር የሚረዳን እውነተኛ ባልንጀራ እስኪሰጠን መጸለይ ሊያስፈልገን ይችላል፡፡ የኔ ጉዳይ ለየት ያለ ነው ማለት የለብንም፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

## 4. *የምናደርገውንና የሚደርግልንን አስተዋጽዖ ለይተን እንወቅ...*

- ኤልያስ ባልንጀራ ያስፈልገው ነበርና እግዚአብሔር ኤልሳዕን አዘጋጀለት። ለዳዊትም ዮናታንን እንዲሁ!
- በሚያስፈልገው የሚያግዘን ማነው? ለሚያስፈልገን ነገር እንደምንጸልየው ሁሉ ለዚህ እንጸልይ።

## 5. *ሌሎችን የምናገለግልበት አቅጣጫ እንንደፍ*

- ‹‹ *ሥራውንም ሠራን ከማለዳ ወገግታም ጀምሮ ከዋክብት እስኪወጡ ድረስ እኵሌቶቹ ጦር ይይዙ ነበር። ደግሞም በዚያ ጊዜ ሕዝቡን፦ ሁላችሁ ከብላቴኖቻችሁ ጋር በኢየሩሳሌም ውስጥ እደሩ በሌሊትም ጠባቂዎች ሁኑልን፥ በቀንም ሥሩ አልኋቸው። እኔና ወንድሞቼም ብላቴኖቼም በኋላዬም የነበሩት ጠባቂዎች ልብሳችንን አናወልቅም ነበር።*›› **ነህ** 4፡21-23።
- እያንዳንዱን ሰው እንዲሠራ እንዲያገለግል አደረገው። የምትሠሩት ባይኖር ተመልከቱ ጸልዩ፣ ተከታተሉ።
- እጅ የመስጠት ተስፋም የመቁረጥ ፈተና ሲያጋጥመን ሌሎች ተስፋ የቆረጡ ሰዎችን እናገልግላቸው፤ እንዴት አድርገን እኔ ከሚለው ስሜት ወጥተን እኛ ወደ ማለት እንደምንደርስ እጅ ከመስጠትና ተስፋ ከመቁረጥም እንደምንገላገል እናየዋለን። እግዚአብሔር ሆስፒታልና ማረሚያ ቤቶችን ከጤንነትና እንደልብ ከመውጣትና መግባን ጎን ያኖራቸው ስንቸገር ለሌሎች በማድረግ ከችግራችን እንድንወጣ ነው። ባለፈውና ሳምንትና በዛሬው ትምህርታችን ነህምያ ምዕራፍ 4 ላይ የሚገኘውን ነቀፋንና እጅ መስጠትን ተስፋ መቁረጥን እንዴት እንደምንቋቋማቸውና በአሸናፊነትም እንዴት እንደምንወጣ ተመልክተናል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ምዕራፍ አምስትን ሳምንት እንማራለን። የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን።
- **መልካም የአባታችን የአቡነ አረጋዊ በዓል ይሁንልን።**

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org